www.xtrapapers.com



Diploma Programme
Programme du diplôme
Programa del Diploma

# Amharic A: literature – Standard level – Paper 1
# Amharique A : littérature – Niveau moyen – Épreuve 1
# Amhárico A: literatura – Nivel medio – Prueba 1

Friday 8 May 2015 (afternoon)
Vendredi 8 mai 2015 (après-midi)
Viernes 8 de mayo de 2015 (tarde)

1 hour 30 minutes / 1 heure 30 minutes / 1 hora 30 minutos

---

## Instructions to candidates

- Do not open this examination paper until instructed to do so.
- Write a guided literary analysis on one passage only. In your answer you must address both of the guiding questions provided.
- The maximum mark for this examination paper is **[20 marks]**.

## Instructions destinées aux candidats

- N’ouvrez pas cette épreuve avant d’y être autorisé(e).
- Rédigez une analyse littéraire dirigée d’un seul des passages. Les deux questions d’orientation fournies doivent être traitées dans votre réponse.
- Le nombre maximum de points pour cette épreuve d’examen est de **[20 points]**.

## Instrucciones para los alumnos

- No abra esta prueba hasta que se lo autoricen.
- Escriba un análisis literario guiado sobre un solo pasaje. Debe abordar las dos preguntas de orientación en su respuesta.
- La puntuación máxima para esta prueba de examen es **[20 puntos]**.

2215 – 0011



© International Baccalaureate Organization 2015

International Baccalaureate
Baccalauréat International
Bachillerato Internacional

www.xtrapapers.com



ከሚከተሉት ምንባቦች **አንዱን** መርጠህ ስነጽሁፋዊ ትንታኔ ስጥ:: ከታች የተቀመጡትን ጥያቄዎች መመለስ ይኖርብሀል::

**1.**

ዱላ.. ከንተሮ.. ጣምራ-ጦር
ሾተሎች የፈለቀብሽ
ባዳፍኔ.. በመትረየስ ላይ
በታንክ ላይ ድል የነሱብሽ::
በከለቻው.. በጡሩሩ
በወርቅ-ጋሻው.. የጧት ጮራ
በቤነቻው ላይ ሲያበራ
የቡልቅታው.. ፀዳሉ
ገና ከሩቁ ሲጣራ::
ነጋሪቱ.. መለከቱ
ሽለላና ቀረርቱ…
ሁሉም አንድ ሆነው ዘመቱ
ለእናት አገር ክብር ሲሞቱ::
በታክቲክ… በስትራቴጂ
በሰለጠነ ሶላቶ
ያልዘመነ ሕዝብ በልህቶ
ድል የነሳብሽ ከቶ
የቦንብ ጋጋታ መክቶ::
አድዋ.. ሰንደቅ ዓላማ
የተናቁ ሕዝቦች አርማ
አድዋ… የአርነት ሽማ
አድዋ.. የአፍሪካ ግርማ::
የክተት ጡሩምባ አንካሮ
የአዋጅ ነጋሪት ተወግሮ
አብጅር.. ቱ ቱ ቱ አብጅሮ
እናት አገርህን አርክሶ
ድንበሯን በጉልበት ጥሶ
ሕልውናዋን ገርስሶ…
መብት-ነፃነትህን ደምስሶ
ጠላት ገባልህ ገስግሶ!
የሚል አዋጅ ሲነገር
ዐይኑ ይቀላል የባላገር::
የጀግና ልቡ ሳይፈተሽ
ወኔና አሞቱ ሳይለካ
በስመ-ያልሰለጠነ
በስመ-ጨለማ አፍሪካ::
በጀግኖች አገር የፈለቅህ
ጀግና መሆንህን እረስቶ
ቅኝ ግዛት አርጎ ሊገዛህ
የመጣን ጣሊያን-ሰላቶ
ያባረርህ የአድዋው አቶ::

*አያልነህ ሙላቱ፣ ከድጡ ወደ ማጡ፣* (2012)::

www.xtrapapers.com



(a) በግጥሙ የአድዋ ጦርነት የቀረበበትን መንገድ አስረዳ::

(b) ፀሀፊው ዘይቤን መጠቀሙ ያስገኘለት ፋይዳ ምን እንደሆነ አብራራ::

www.xtrapapers.com



**2.**

በአንድ የገጠር ደብር አንድ ዋቂ ሊቅ ነበሩ:: እኚህ ይህ ቀረህ የማይባሉ ሊቅ ምንም ዓይነት ስሕተት አያልፉም:: ባገኙት አጋጣሚ ሁሉ ስሕተቶችን ያርማሉ:: እርሳቸው ለሰው ሳይሆን ለእውነት የቆሙ ነበሩ:: የጎደለ ካለ ይሞላሉ:: የተጣመመ ካለም ያቃናሉ:: ታላቅ ነው ብለው አይፈሩም ታናሽ ነው ብለው አይደፍሩም::

አንድ ጊዜ አንድ ተምሬያለሁ ያለ ብርሌ የሚባል ሰው እዚያ ደብር ይቀጠራል:: ታድያ ብርሌ ዕውቀት በዞረበት የዞረ አይመስልም:: ያልተማረውን ሳይሆን የተማረውን መቁጠር ይቀላል:: እንኳን ምስጢር ሊያደላድል ንባብ አይሆንለትም:: ነገር ግን “አላዋቂነትን ምላስ፣ ቁስልን ልብስ ይሸፍነዋል” እንደሚባለው ነገር እንደ ተልባ የሚያንጣጣ ኃይለኛ ምላስ ነበረው:: ለሊቃውንቱ የሚሆን ቢያጣ ለባ ልቴቶች የሚሆን ነገረ ዘርቅ ነበረውና ሠፈሩን ሁሉ በአንድ እግሩ አቆመው:: ሴት ወይዘሮው ወንድ መኳንንቱ ሁሉ እጅግ ወደደው::

ታድያ ብርሌ ጠዋት ጠዋት የሰው ትኩረት እስባለሁ ብሎ ተአምረ ማርያም ሊያነብ ይነሣል:: ከዚያም ድምፁን ከፍ አድርጎ “ተአምሪሃ” ይላል “ሃ”ን ወደ ላይ እያነሳ:: ሊቁም አትሮንሱ አጠገብ ተቀምጠው “ማርያም አትነሳም፣ ቀጣይ ናት” ይሉታል:: በግእዝ ንባብ ሕግ “ማርያም” የሚለው ስም ሲነበብ ንባቡ ይወርዳል እንጂ አይነሣም ማለታቸው ነው:: ብርሌም በአላዋቂነቱ ሳያፍር “አለመማሬ በሕዝብ ፊት ተገለጠብኝ” ብሎ ቂም ይይዛል:: ሊቁ በየገዜው ንባቡን እያረሙ አስቸገሩት::

ብርሌ ሊቁን የሚበቀልበት ተንኮል ሠራ:: ተአምረ ማርያም ማንበቡን ተወ:: ምእመናኑ ቅሬታ ተሰምቷቸው ጠየቁት:: እርሱም በየምእመኑ ቤት እየዞረ “እኔ ተአምረ ማርያም ሳነብብ ሊቁ የማርያ ምን ስም አታንሣ ስላሉኝ ነሠ” እያለ አድማ ቀሰቀሰ። የማያስተውል ሕዝብና ኮለል ያለ ውኃ በፈለጉት መንገድ ይነዳልና ሕዝቡ በሊቁ ላይ ቂም ያዘባቸው::

አንዳንድ ምእመናንም ለብርሌ “እስኪ እርስዎ ተአምሩን ያንብቡና ሊቁ የማርያምን ስም አታ ንሣ ሲሉዎት እንስማ?” አሉት:: ብርሌም እሺ ብሎ በቀጣዩ ሰንበት ከቅዳሴ በኋላ ተአምረ ማርያሙን አውጥቶ “ተአምሪሃ” ብሎ ንባቡን አንሥቶ አነበበው:: ሊቁም እንደ ልማዳቸው “ማርያም አትነሣም” ይሉና ያርሙታል:: ብርሌም ወደ ሕዝቡ ዞሮ “ይኸውላችሁ ምእመናን ማርያምን አታንሣ እያሉ እኔ ማንበብ አልቻልኩም” አለና ተናገረ::

ሕዝቡም “ሆ” ብሎ በሊቁ ላይ ተነሣ:: “ከደብሩ ካልወጡ” ብሎም አመጸ:: ሊቁም ማወቃቸው ጥፋት ሆኖ ባልተማሩና በማያስተውሉ ሰዎች ግፊት ደብሩን ለቅቀው ሔዱ::

ለመሆኑ እንዴት ነው መስማት ያለብን? የምንሰማቸው ነገሮች ሁሉስ ትክክል ናቸውን? መም ህር ደጉ ዓለም ካሣ “እውነትን የሚያስንቅ ውሸት፣ መውጋትን የሚያስንቅ መሳት አለ” ይላሉ:: ፎርጅድ ብር ከእውነተኛው ብር የተሻለ መልክና ንጽሕና አለው:: ታድያ የዋሓን እንዴት እንለየው? አንዳንድ ጊዜ ለውሸትም ማስረጃ የሚመስል ነገር ሊኖረው ይችላል::

ዳንኤል ክብረት፣ የኔ ጀግና ና ሌሎች፣ (2012)::

(a) በቅንጭብ ጽሁፉ ውስጥ የምሁሩ ባህሪ እንደምን ቀረበ?

(b) ግጭት ለጽሁፉ ያለውን ጥቅም አስረዳ?